# የአትላንታ  ብስረተ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን የደብሩ አለቃ በወያኔው ጳጳስ አቡነ ፋኑኤል ዳግማዊ ቁሊንቢ ገብርኤል ተብሎ እንዲጠራ አስወሰኑ

ከምዕመናን

በአለፈው ሳምንት የቅዱስ ገብርኤል የሐምሌ 19  ዓመታዊ ብዓል በአትላንታ ተከብሮ ውሏል። በዚህም የቅዱስ ገብርኤል በዓል ላይ የወያኔው አገልጋይ ሲኖዶስ የፓትርያርክ ተወካይ አቡነ ፋኑኤል የተባሉ የብዙ ማዕረግ መጠሪያ ስም ያላቸው የዋሽንግተን ዲሲ አካባቢ አገረ ስብከት የተገኙበት ነበሩ። የፓትራያርኩን የአባ ማቲያስ ስም በቅዳሴ ካልጠራሁ ሞቼ እገኛለሁ ያሉት የደብሩ አለቃ ቄስ አዲስ ይልማ ቸርነት አልቅሰውና ፍቅር ፍቅር በማለት ምእመናንን በመስበክና ጫና በማድረግ ከጥር ወር ጀምሮ አሳባቸው ተሟልቶ የአባ ማቲያስን ስም በቅዳሴ የጠሩ ሲሆን አሁን ደግሞ ይግረማችሁ ብለው ከእምነት በራቀ አስተሳሰባቸው፣መንፈሳዊ አስተዋይነትን ያላገናዘበ፣የምእመናን እምነትና ስሜትን ባላካተተ ሁኔታ የብስራተ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያንን ዳግማዊ ቁሊቢ ገብርኤል ይባልልኝ ብለው ከላይ በተጠቀሱት ካህን ቡራካ አስወሰኑ።ትንሽ ቆይቶስ ምን ይሰማ ይሆን?

እግዚአብሔር ያሳያችሁ ! ይህ ቤተክርስቲያን በብፅዕ ጳጳስ አቡነ ይሥሃቅ (አልፈዋ ነብሳቸውን ለገነት ያርገው) ከአስር ዓመት በፊት ቡራኬ ተቀብሎ የተከፈተና ስንገለገልበት የቆየ ነው። ዛሬ የኛን አባት ቡራኬ በመጣስ ሌላ ተጨማሪ በወያኔ ጳጳስ መደረብ ምን ማለት ነው? ይህ እኮ የእግዚአብሔር ቅዱስ ቤት ነው፣ የመልዓኩ ቅዱስ ገብርኤል ስም ነው! የወያኔ ፖለቲካ ማራመጃ፣ የንጽህ ፣የዋህ ምእመናን በፍቅር ስም ማነኋለል መልካም አይመስልም። ብዙ ምእመናን አዝነዋል ተገርመዋል።

የቤተክርስቲያን ስም በጳጳስ ቡራኬ ከተፈቀደ በኃላ ሌላ መጠሪያ ወይንም ተለጣፊ ስም ሲወጣለት ሰምቼ አላውቅም። ዳሩ ግን ለባለ ሥልጣናት የሚያገለግል፣ከወያኔ ጋር የዋለ፣ የእግዚአብሔርን መንገድ የሳተ ሥርዓት፣ እምነትን ያዛባና የሃማኖቱ እምነት ስው፣ወገንተኛ፣ጥቅምና አሸርጋጅ ከሆነ እጅግ ከርማል። ይህ ዳግማዊ  ቁሊንቢ እንዲባል የተፈለገበት ምክንያት፣ አንድ ይህ ቤተክርስቲያን የዛሬ አስር ዓመት በብፁዕ ጳጳሳ አቡነ ይሥቅ መልካም ፈቃድና ቡራኬ የተከፈተ ነበር። እኚህ አባት፣ ፓትርያርክ በሕይወት እያለ ሌላ አይመረጥም፣የቅኖናውን ሕግ አታፍርሱ በማለት ለሲኖዶሱ በማሳሰብና የወያኔውንም ወራሪ ኃይል በሃይማኖት ጣልቃ ገብነት አውዘውና ገዝተው ወደ ውጭ ተመልሰው ይኖሩ ነበር።በዚህ ሁኔታ የወያኔ ዳጋፊዎች የአቡነ ይሥአቅን ሥራ ለማጥፋት ይፈልጋሉ።በዚህ የተነሳ የብስራተ ቅዱስ ገብርኤል ስም በቁሊንቢ ገብርኤል በተለምዶ እንዲዋጥና እንድረሳ ነው።ሌላውና ዋና ምእመናኑን ደካማና ተላላ በማድረግ ቁሊንቢ ገብርኤል የብዙዎች ስለት ተሰምቷል፣ተዓምር አሳይቷል ስለሚባል፣ የአትላንታውም ቅዱስ ገብርኤል ይህን ስም ቢያገኝ በምእመናኑ  መንፈስ  ውስጥ በማስገባት፣ ከዚህ አገኘነው በማለት

ብዙ ሰዎች ወደኛ ይጐርፋሉ፣ ብዙ ገንዘብ እናገኛለን ከሚል ከወያኔዊ አስተሳሰብ የመነጨ፣ የእግዚአብሔርን ፣የክርስትና ሃይማኖት መንገድ የተጻረረ ከንቱ ንዋዬ መናፍቅ ውጥን ተደርጐ ነው። በሦሥተኛ ደረጃ በስደት ያለውን ሲኖዶስ በዚህ በአትላንታ ለመጻረንና ክፍፍልን ለማጎልበት ነው። ለዚህም መረጃው በወያኔው ፓትርያርክ እምነት ያላቸው በአቡነ ፋኑኤል የሚመራው የአቦይ ገብረ መንፈስ ቅዱ ቤተክ አባላት በሙሉ በዚህ በዓል ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ መገኘት ነው። ምን አፋቀራቸው? የእግዚአብሔር ፍቅር፣አምልኰት ወይስ የሰው? ይህን ክርስቲን ያስተውለው።

በእውነት እግዚአብሔርን አንድ አምላክ ያደረገና በንጹህ፣ በቅን ልብ ያመነ በቦታ ወይንም በስም አሰያየም አያምንም። ቅዱስ ገብርኤል አንድ ነው ቦታም አይወሰነውም።ስም አይገድበው።እምነትም በእግዚአብሔር እንጂ በሰው ፣ ለሰው ማሸርገድ አይደለም።የነዚህ ካህናት እምነት ፣አካሄድና አፈጻጸም እጅግ የሚያስፈራና የሚያሳስብ ጉዳይ ነው። እግዚአብሔር ይርዳን።

በዚህ ብስራተ ቅዱስ ገብርኤል የመንፈሳዊ መምህር የሆኑት ከስድስት ወር በፊት እደመጡ ዋና ሥራቸው ያደረጉት የአባቶቼን ስም በቅዳሴ ጠርቼ መቀደስ አለብኝ፣ አመመኝ በማለት ምእመናኑን በመወስወስ፣ በማሳዘን ጥቂቱን ሲይዙ ብዙ ወደሌላ ቤተክርስቲን ሄደዋል። አባቶቼ የሚባሉት እነማን ናቸው? እነአባ ማቲያስ? አነ አባ ጳውሎስ? የነዚህን የወያኔ ተመራጮችና ሕዝብ፣ አገር አስጠፊዎች !! ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ ነው። በዚህም በዓል ላይ በአብዛኛ የተሰበከውና ትምህርት የተሰጠው ለኝህ ያላባቶቼ ስም አመመኝ፣ ወደ አገር እመለሳለሁ ስለአሉት ቄስ ነበር ምስክርነት የተሰማው።አባ ፋኑኤል በምክርና በማበረታታት ብዙ እደመከሯቸው በመናገር አንድነታቸውን ሲአረጋግጡ ከአቦይ የመጠትም ካህን አንድነታችን ጠንክሯል በማለት ወያኔዊ ፍቅራቸውን አጠናክረዋል። ቄሱም ከዚህ በኃሏ አልመለስም በማለት ደጋግመው በፉከራ መልክ በማሰማት የዋሁን ምእመናን አስጨብጭበዋል።

ከዚህም በማከታተል የተደረገው የብዓሉ መልዕክተ፣ ቤተክርስቲያኑን በተሻለና በኢትዮጵያ ቤተክርስቲን መልክ በጉልላት እዲስራ ገንዘብ ማሰባሰብ ነበር ።በኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት እጅግ ትልልቅና ድንቅ የሆኑ ቤተክርስቲያኖች እየተሰሩ ነው።እዚህም በውበት ያማሩ ቤክ መስራት አለብን፣ ሲታመሙ ሁለት ሦሥት ሺህ ለህክምና ከምታጠፉ፣ ወይም ከዚህ ስትወጡ ፖሊስ ትኬት ቢሰጣችሁ ብዙ ትከፍላላችሁ፣ለቅዱስ ገብርኤል ስጡ ይጠብቃችኋል እየተባለ ነበር ጥያቃውና ማሳሰቢያው። አወ ቅዱስ ገብርኤል ያድናል፣ ይጠብቃል። ነገር ግን ጥያቄው ወይም ማሳሰቡ ከማስፈራራት ጋር ለምን ይሆናል? ይህ እኮ ከልት ነው አጉል እምነት። አቡነ ፋኑኤል ገንዘብ ማሰባሰቡን በተመለከተ፣ ይህ ቤተክርስቲያን ኢትዮጵያ ውስጥ የሰንበቴ ቤት ነው የሚመስለው ከዚህ በተሻለ ማሰራት አለባችሁ በማለት አናንቀው ነው ምእመናኑን ያሳሰቡት።ሕዝበ ክርስቲያን እግዚአብሔር ያሳያችሁ ! ሃቁ ፣እውነቱ የት ነው? ኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ወቅት ብዙ አበያተ ቤተክርስቲያኖች ፈርሰዋል፣ ዝናብ ገብቶበታል ወይም ተቃጥለዋል፣ ገዳሞች ታርሰዋል፣ አባቶች ታስረዋል ፣ተገለዋል። የአዲሳባው ሲኖዶስ ግን ቤት እያስራ ያከራያል። ምእመናን እያዋጡ ነው በአብዛኛው የሚሰራው። እስልምና እየተስፋፋ፣ ክርስትና ሃይማኖት ግን ችግር ላይ ነው። እዚህ ደግም የሚሰበከውን ተመልከቱ።

እምነት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ፣ እምነት እውነት ላይ የተመሰረተ ፍቅር ነው ለዚህ በፅናት እያስተዋሉ መቆም ነው።እምነታችን በአንድ አምላክ ብቻ ነው። በክርስትና ሃይማኖት ላይ ጥቃት እየደረሰ ነው። እናስተውል። **እግዚአብሔር ኢትዮጵያና ሕዝቧን ይጠብቅ አሜን !**